# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 338 ጥቅምት 22 2007


በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዉስጥ በንጹሃን ዜጎቻችን ህይወት ላይ እየፈጸመ ያለዉ ግፍ በአገራችን ህዝብ ላይ ሲደርስ የመጀመሪያዉ አይደለም፤ ካላቆምነዉ በቀር የመጨረሻዉ እንደማይሆንም አካሄዱ በግልጽ እያሳየን ነዉ። ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ ለምለም መሬት እየፈለገና ነዋሪዉን እያፈናቀለ መሬቱን ለባለሚሎቹ ማደሉን ሳይታቀብ በማንለብኝነት እንደቀጠለበት ነዉ። መሬቱን የተቀማዉ ደሃዉ የጋምቤላ ገበሬም ጫካ እየገባ ከወያኔ ጋር መተናነቁን ቀጥሏል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ላለፉት 3 ወራቶች ያሰለጠናቸውን የአምስተኛ ዙር ታጋዮች አስመረቀ

አገራችን ኢትዮጵያ በጎጠኛውና በከፋፋዩ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ መዳፍ ውስጥ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ የደረሰባትንና እየደረሰባት ያለውን ውርደትና መከራ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመገርሰስ ወደ ክብር ለመለወጥ፤ ብሎም የናቋትን እና ያዋረዷትን ጉጅሌዎች በፍትህ ሚዛን ላይ እንዲቀመጡና ፍርዳቸውን እንዲያገኙ ማድረግን ቀዳሚ አላማው አድርጎ ወደ ዱር የከተተውና፤ በአገራችን የነገሰውን ፍጹም አምባገነናዊ አገዛዝ በሚገባው ቋንቋ ሁሉ ለማነጋገር እጅግ በዘመነ ሁኔታ እየተደራጀ የሚገኘው የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል 5 ዙር ታጋዮችን ሰኞ ጥቅምት 17 ቀን 2007 ኢ.ም ማስመረቁን ከህዝባዊ ሃይሉ የተላከልን መረጃ ያመለክታል። ተመራቂ ታጋዮቹ ላለፉት 3 ወራት በተከታታይ በወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የመረጃ እና ደህንነት ትምህርቶች በበቂ ሁኔታ መሰልጠናቸው የተገለጸ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ያለውን የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ወቅቱ የሚፈልገውን ቴክኖሎጅ በመጠቀም መረጃን መቀበልና ማስተላለፍን የጨመረም እንደነበር ተያይዞ ተጠቅሷል።

በምረቃ ስነስርዓቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የህዝባዊ ሃይሉ ዋና አዛዥ ኮማንደር አሰፋ ማሩ የህዝባዊ ሃይሉን ወቅታዊ አቋም በተመለከተ ሲናገሩ "ህዝባዊ ሃይላችን በኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋውን ዘረኛና አፋኝ የወያኔ አገዛዝ ከህዝባችንና ከአገራችን ጫንቃ ላይ አስወግዶ በምትኩ ፍትሃዊ ና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ከተመሰረተ ጀምሮ ባለፉት ጥቂት አመታት በርካታ ስራዎችን በመስራት አሁን አስተማማኝ ድርጅታዊ አቋም ላይ ይገኛል" ሲሉ በምረቃው ስነ ስርአት ላይ ለተገኙት ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ጋምቤላ ዉስጥ ከ 50 በላይ የልዩ ሃይል ወታደሮች ከነ ትጥቃቸው መሰወራቸው ተሰማ

በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ አጋዚዎችና በሸኮ መዠንገር ጎሳ ታጣቂዎች መካከል የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ ቁጥራቸው 50 የሚጠጋ የአገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊስ፣ የመከላከያና የአካባቢው ሚሊሺያዎች መገደላቸውን ተከትሎ በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት መንገሱንና አሁን ድረስ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአጋዚ ጦር ወደ ስፍራው እየተንቀሳቀሰ መሆኑን እየተከታተልን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ በክልሉ በጨፍጫፊውና ፋሽስታዊው አገዛዝ የተማረሩ ቁጥራቸው ከ 50 በላይ የሆኑ የልዩ ሃይል ወታደሮች ከነ ሙሉ ትጥቃቸው አገዛዙን ከድተው ከአካባቢው መሰወራቸውን ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል።

የከዱት የልዩ ሃይል አባላት የአኝዋክ፣ ኑዌርና መዠንገር ጎሳ ተወላጆች መሆናቸው የተመለከተ ሲሆን በተለይ የነዚህ ጎሳ ተወላጅ የልዩ ሃይል አባላት የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ወገኖቻቸው ላይ እየወሰደ ባለው አረመኔያዊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ማለትም የጅምላ ግድያና እስር እንዲሁም የማፈናቀል ወንጀል እጅግ መማረራቸው ለማወቅ ተችሏል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የክልሉ ቅጥረኛ ሹማምንት በልዩ ሃይል አባላቱ መከዳት መደናገጣቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን አሁንም ሊከዱ የሚችሉ አባላት ይኖራሉ በሚል ስጋት ተወጥረው እንደሚገኙና በልዩ ሃይል አባላቱ ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር እያደረጉ እንደሚገኙ ታውቋል። ይሁን እንጂ ዘጋቢያችን የውስጥ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ ያደረሰን መረጃ እንደሚያሳየው በክልሉ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የልዩ ሃይል እንዲሁም የፖሊስ አባላት ከፋሽስታዊው አገዛዝ ጋር ተቃቅረው እንደሚገኙና ከድተው ለመውጣት ምቹ ሁኔታዎችን እየተጠባበቁ እንደሚገኙ አመልክቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን በመክዳት የሚሰወሩ የመከላከያ፤ ፖሊስ እንዲሁም የልዩ ሃይል አባላት እጅግ እየተበራከቱ መምጣታቸውን እየተከታተልን መዘገባችን አይዘነጋም።

## የወያኔ ሽብር ከፍተኛ ስጋት ላይ እንደጣላቸዉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ተናገሩ

አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ እንደለመደው የፈጠራ ድራማውን ለማቀናበር ይረዳው ዘንድ የሽብር ጥቃት በአዲስ አበባ በተለይም በቦሌ አካባቢ ሊፈጸም ነው በሚል ህዝብን በማሸበር ስራ ላይ መጠመዱን ተከትሎ ነዋሪዎች አገዛዙ እያደረገ ባለው አሰልች ፍተሻ እና እየነዛው ባለው ዲስኩር ስጋት ላይ መውደቃቸውን በመግለጽ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

በአዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታየው ፍተሻ ሰኞ እለት ተጠናክሮ መቀጠሉ የታወቀ ሲሆን በተለይ በቦሌ አካባቢ ነዋሪዎችና አሽከርካሪዎች አሸባሪዎች ገብተዋልና አጋልጡ በሚል መኪኖች ሲፈተሹ መዋላቸውን፣ መንገደኞች እየቆሙ መፈተሻቸውን እንዲሁም የቤት ለቤት አሰሳ መደረጉንና ለሰአታት ታግተው የቆዩ ነዋሪዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተለይ የአካባቢው ሰዎች አገዛዙ ሆን ብሎ ሽብር በመንዛት ስራችን እንዳንሰራ እያደረገን ነው፣ የሚፈነዳ ነገር ካለም እንደለመደው አገዛዙ ራሱ የሚያፈነዳው ነው ሲሉ በርካቶች ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሽቱ ወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ የፈንጅና የቦንብ ጥቃቶችን በመፈጸም የንፁሃን ዜጎችን ህይወት መቅጠፉ የሚታወስ ሲሆን አገዛዙ ራሱ የፈጸመውን የሽብር ጥቃት ሆን ብሎ በሌሎች ሃይሎች የተፈጸመ እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብና ድራማ በመስራት ርካሽ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ሲንቀሳቀስ እንደነበርም በተለያዩ ጊዜያት መጋለጡ አይዘነጋም።

## አምንስቲ ኢንተርናሽናል በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የሚደርሰዉን ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት በመጥቀስ ሪፖርት አወጣ

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ላይ የእስራት፣ የስቃይ፣ የግድያ፤ የአስገድዶ መደፈር እና ሌሎችም ጭካኔ የተሞላባቸው ዘግናኝ የግፍ ተግባራትን እየፈጸመ ይገኛል ሲል ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምኒስቲ ኢንተርናሽናል ሰኞ ዕለት ባወጣው ሪፖርት ገለጿል። ድርጅቱ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ 2011 እስካሁaን ያለውን ሁኔታ አጥንቶ ይፋ ባደረገው ሪፖርት፣ ቁጥራቸው ከ 5 ሺ በላይ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያን በእስር ላይ እንደሚገኙ በማመልከት በእስር ላይ የሚገኙት ሰዎች የግድያ፤ የከፋ ስቃይና ሰቆቃ እንዲሁም በሴት እህቶቻችን ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደሚፈጸሙባቸው ተመልክቷል "ምክንያቱም ኦሮሞ በመሆኔ" የሚል ርዕስ የተሰጠዉ የዓለማቀፉ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት አምኒስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ከ200 በላይ ሰዎች ምስክርነትን በማየት ሰነዱ እንደተዘጋጀ የተመለከተ ሲሆን ፋሽስታዊው አገዛዝ ገበሬዎችን፤ አስተማሪዎችን፤ የጤና ባለሙያዎችን፤ የአገዛዙ ተቀጣሪዎች ሳይቀር በዘፈቀደ አስሮ የከፋ ስቃይ እየፈጸመባቸው እንደሚገኝ ጥናቱ አጋልጧል።

መቀመጫውን በእንግሊዝ ያደረገው አምንስቲ ኢንተርናሽናል አብዛኛውን ለእስር ተዳርገው የከፋ ስቃይ እየተፈጸመባቸው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አዲስ አበባ ዉስጥ በሌሊት በሚለጠፉና በሚበተኑ የታቀዉሞ ህዝብ ጽሁፎች የተነሳ ወያኔን ውጥረት ውስጥ መግባቱ ታወቀ

ዛሬም አዲስ አበባ ከቦሌ ወሎ ሠፈር እስከ ደምበል አካባቢ በወረቀት ላይ በተፃፉ መፈክሮችና ተቃውሞዎችን የሚያስተጋቡ ጽሁፎች ተለጣጥፈውና ተበትነው መገኘታቸውን ተከትሎ አገዛዙ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መግባቱን የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። የውስጥ ምንጫችን እንዳመለከተው የተቃውሞ መፈክሮቹ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያነሳቸውን የመብት ጥያቄዎች እንዲመለሱ የሚጠይቁ መሆናቸውን ያደረሰን ሲሆን መብትን መጠየቅ ሽብር አይደለም፣ ድምጻችን ይሰማ፣ በአገዛዙ ጥቁር ሽብር ተስፋ አንቆርጥም የሚሉ መፈክሮች በየመንገዱ ተለጥፈው ታይተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በተለይ በቦሌ ክፍለ ከተማ ለሚገኙት የቀበሌ ጽ/ ቤቶች እና በቀበሌዎች ለሚሰሩ ቅጥረኛ ካድሬዎች ጭምር ህብረተሰቡን በተለይም የሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ የስለላ ስራ በመስራት ድርጊቱን የሚፈጽሙና የሚያስተባብሩ አካላትን ለህግ እንዲያቀርቡ የሚያዝ አስቸኳይ ደብዳቤ መፃፉን ለማወቅ ተችሏል። አገዛዙ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ እየደረሰበት ያለው ተቃውሞ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የወያኔ ግፍ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

ዘረኛዉ ወያኔና ባለሟሎቹ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጋምቤላና በሸኮ መዠንገር አካባቢ የሚያካሄዱትን የማንአለብኝነት የመሬት ዝርፍያና ዜጎችን እርስ በርስ በማጋጨት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት አራዊታዊ ሩጫ የተነሳ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ህዝብ ይህ ነዉ ተብሎ ሊነገር የማይችል እልቂት እየተፈጸመበት ነዉ። የመዠንገር ህዝብ የሞትና የህይወትን ያክል የማይወጣዉ ምርጫ ስለቀረበለት ተወልዶ ያደገበትን የአባቶቹንና የአያቶቹን አካባቢ ለቅቆ በመዉጣት እራሱን ለመከላከል ባደረገዉ እንቅስቃሴ የብዙ ንጹሃን ዜጎችና ቁጥራቸዉ ቀላል የማይባል ምስኪን ወታደሮችም ህይወት ማለፉ በይፋ እየተሰማ ነዉ። ይህንን ተከትሎ ግፈኞቹ የወያኔ መሪዎች በአካባቢዉ ብዙ ዘመን በቆዩ ብሄሰቦች መካከል ሆን ብለዉ ግጭት እንዲነሳ እያደረጉ በህዝብ መካከል ግጭትትና ዕልቂት የተነሳ በማስመሰል በአካባቢዉ ከፍተኛ ሰቆቃ በመፈፀም ላይ ይገኛሉ።

በዚህ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች እየደረሰ ላለዉ መጠነ ሰፊ ግጭትና ዕልቂት ተጠያቂዉ በአካባቢዉ ለዘመናት አብሮ በመደጋገፍ የኖረዉ ህዝብ ሳይሆን የዚህ አሰቃቂ ዕልቂት ባለቤትና ጠንሳሽ ህወሓትና ዘረኛ መሪዎቹ መሆናቸዉን ለአንድም ደቂቃ ሊዘነጋ አይገባም። ይህ ግጭት ሊነሳ የቻለዉ ህወሓት የአካባቢዉን ደሃ ገበሬ ከትዉልድ መሬቱ ላይ እያፈናቀለ መሬቱን ለከፍተኛ የጦር መኮንኖቹና የኔ ለሚላቸዉ ባለሟሎቹ በማከፋፈሉ መሆኑን ይህንን ግፍ የሚሰማ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልብ ሊለዉ ይገባል። ህወሃት የአማራን ተወላጆች አካባቢዉ የእናንተ አይደለምና ዉጡ እያለና እያፈናቀለ በሌላ በኩል ግን በየክልሉ የአካባቢዉን ነዋሪ እያፈናቀለ የራሱን ሰዎች የመሬት ባለቤት ማድረጉ አዲስ የጀመረዉ ክስተት ሳይሆን ቆየት ያለና ስር የሰደደ የወያኔ አሰራር ነዉ።

ይህ ዛሬ በጋምቤላና በአካባቢዋ እየደረሰ ያለዉ ግፍና መከራ ለአካባቢዉ ህዝብ ብቻ የሚተዉ ነጠላ ችግር ሳይሆን በአጠቃላይ ወያኔ በአገራችን ላይ ሆን ብሎ በማድረስ ላይ ያለዉ ችግርና መከራ አካል ነዉ። በጋምቤላ ዉስጥ የፈሰሰዉና እየፈሰሰ ያለዉ የሴቶች፤ የወጣቶች፤ የአረጋዉያንና የህጻናት ደም ለሁላችንም የነጻነት ጥሪ እያቀረበልን ነዉ። ይህ የነጻነት ጥሪ ሰምተን የምናልፈዉ ወይም ነገ እንደርሳለን በለን በቀጠሮ የምናልፈዉ ጥሪ አይደለም። ጥያቄዉ የአገርና የዜጎች ህልዉና ጥያቄ ነዉና ነገ ዛሬ ሳንል አሁኑኑ ይህንን የነጻነት ጥሪ ሰምተን ምላሽ ልንሰጠዉ ይገባል።

ይህ ወያኔ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዉስጥ በንጹሃን ዜጎቻችን ህይወት ላይ እየፈጸመ ያለዉ ግፍ በአገራችን ህዝብ ላይ ሲደርስ የመጀመሪያዉ አይደለም፤ ካላቆምነዉ በቀር የመጨረሻዉ እንደማይሆንም አካሄዱ በግልጽ እያሳየን ነዉ። ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ ለምለም መሬት እየፈለገና ነዋሪዉን እያፈናቀለ መሬቱን ለባለሟሎቹ ማደሉን ሳይታቀብ በማንለብኝነት እንደቀጠለበት ነዉ። መሬቱን የተቀማዉ ደሃዉ የጋምቤላ ገበሬም ጫካ እየገባ ከወያኔ ጋር መተናነቁን ቀጥሏል። ትናንት በኦሮሚያ፤ በጉራፈርዳና በቤንሻንጉል አካባቢዎች በአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰዉ ግፍና መከራ ዛሬ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ ብሄረሰቦች ላይ እየደረሰ ነዉ።

ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ ይህ ለከቱን የለቀቀ የህወሓት ዕብሪት እንዲተነፍስና በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰዉ ግፍና ሰቆቃ እንዲቆም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነግ በኔ እያለ የነጻነት ትግሉን እንደቀላቀል የትግል ጥሪ ያደርጋል። ወያኔ እያደረሰ ያለዉ እስራት፤ ድብደባ፤ ግድያና ስደት የሁላችንንም ቤት እያንኳኳ ነዉና ሁላችንም እንደ አንድ ሰዉ ቆመን ወያኔንና ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐት በትግላችን መደምሰስ አለብን። በጋምቤላና በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የፈሰሰዉ የንጹሃን ወገኖቻችን ደም ደመከልብ ሆኖ የማይቀረዉ ለመብታችንና ለነጻነታችን ቆመን ወያኔን ካስወገድን ብቻ ነዉ።

**በህብረት እንነሳ!!!!**

---

## የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል ላለፉት 3 ወራቶች ያሰለጠናቸውን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የክብር እንግዶች ተናግረዋል። ኮማንደር አሰፋ ማሩ አያይዘው እንደገለጹት "ይህን የአምስተኛ ዙር ምርቃት ከቀደምቶቹ 4 ዙር ምርቃቶች የሚለየው የኢትዮጲያ ህዝብ አርበኞች ግንባር፣ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ እና የግንቦት ሰባት የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ተዋህደው ባንድ ድርጅታዊ ጥላ ስር ትግላቸውን አስተባብረው ለመታገል የሚያደርጉትን የውህደት ሂደት የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ያደረሱበት ወቅት ላይ መደረጉ ነው " ሲሉ አስረድተዋል።

ኮማንደሩ በስተመጨረሻም "ይህ የህዝባዊ ሃይላችን ስልጠና በግንቦት ሰባት ስም ከሚደረጉት ስልጠናዎች የመጨረሻው ይሆናል በማለት የገለጹ ሲሆን ለተመራቂ ታጋዮች ባስተላለፉት መልዕክት "ስልጠና ላንድ ታጋይ የትግሉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሲሆን በስልጠና ላይ ያገኛችሁትን ትምህርት በተግባር ለቆምንለት ዓላማ እና ተልዕኮ በቁርጠኝነት እንደምታውሉት ሙሉ እምነቴን እገልጻለሁ" ካሉ በኋላ የአገርና የትውልድ ጠላት የሆነውን የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርገን ለማስወገድ በምናደርገው እልህ አስጨረሽ ትግል አብረን እንቁም፤ ሕዝባዊ ሃይላችንንም ተቀላቀሉ ሲሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ወገናዊ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል በሀገር ውስጥ እንደማእበል እየገነፈለ ያለውን የአታግሉን የሕዝብ ጥያቄ በተደራጀና በተቀነባበረ መንገድ በተገቢው መልኩ ለማስተናገድ እንዲችል እንደ ድርጅት ከመቼው ጊዜ በላይ ራሱን እያደራጀና እያጠነከረ እንደሚገኝና ምቹ አታጋይ ተቋም ሆኖ ለመውጣት ሌት ተቀን እየደከመ የሚገኝ ድርጅት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህ ቀደም በ 4 ተከታታይ ዙሮች በርካታ ታጋዮችን ማስመረቁን መዘገባችን አይዘነጋም።

## አምንስቲ ኢንተርናሽናል በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የሚደርሰዉን ከፍተኛ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሚገኙት የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባርን ትደግፋላችሁ በሚል መሰረተ የለሽ ውንጀላ እንደሆነ ተመልክቷል። በግፍ ከታሰሩ ኦሮሞች ውስጥ ባሏ በኦነግ የተጠረጠረን ነፍሰ ጡር ሴት ያዋላደ ሃኪም፤ በማዳበሪያ አቅርቦትና ሽያጭ ቅሬታ ያሰሙ በመቶዎች የሚቆጠሩ ገበሬዎች፤ ገበሬዎችን ለአመጽ አነሳስተሃል በሚል መሰረተ ቢስ ክስ የተከሰሰ የግብርና ባለሞያ እንደሚገኙበት ተገልጿል።

በሪፖርቱ ላይ እንደተመለከተው የኦሮሞን ባህል ተግባራዊ የሚያደርጉ በ ብዙ 100 ዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በግፍ ለእስር መዳረጋቸው የተጠቆመ ሲሆን ሰዎቹ ይህን በማድረጋቸዉ አገዛዙን እንደሚፃረሩ ተደርጎ መወሰዱ እጅግ አሳዛኝና ህገወጥ ድርጊት መሆኑ ተመልክቷል። የአምንስቲ ኢንተርናሽናል አጥኚ ክሌር ቤስተን እንደገለጹት የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የኦሮሞ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን የሚያሰቃየዉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎች ናቸዉ በሚል ጥርጣሬ መሆኑን በማመልከት ሰቆቃና ግፉ የሚፈፀምባቸዉ ሰዎች ደግሞ በሁሉም የሙያ መስክ የተሠማሩ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

የአምንስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ ተመራማሪ ክሌር ቤስተን አያይዘው እንደገለጹት የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ላይ እየፈጻማቸው የሚገኙትን እጅግ ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መፍትሄ እንዲያገኙ በተደጋጋሚ ብናሳውቅም ፈጽሞ ፈቃደኛ ባለመሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ሁሉ በየዘርፉ በሰነድ በመያዝ ለአለማቀፍ መንግስታትና ማሕበረሰብ እናቀርባለን ሲሉ መናገራቸው ታውቋል። ኬንያ የሚገኙት የአምንስቲ ኢንተርናሽናል አጥኚ ክሌር ቤስተን አለማቀፉ ማህበረሰብ፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እንዲሁም የአፍሪቃዉ የሰብዓዊ ጉዳዮች ኮሚሽን በአስቸኳይ ነጻ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አጣሪ ቡድን እንዲያሰማሩ ጠይቀዋል።

ይሁን እንጂ የተለያዩ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያንና የፖለቲካ አራማጆች አገዛዙ ወደ እስር በማጋዝ ስቃይ እየተፈጸመባቸው የሚገኙት ኦሮሞዎች ቁጥር በአምንሲቲው ሪፖርት ከተጠቀሰው በእጅጉ እንደሚልቅ ምስክርነታቸውን እየሰጡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ባለፉት 3 አመታት ከ 5 ሺ በላይ ኦሮሞች ለእስር ተዳርገው ስቃይ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ጥናቱ ይፋ ያድርግ እንጂ በተጠቀሱት ጥቂት አመት ውስጥ ብቻ የታሳሪዎች ቁጥር ከ 20 ሺ እንደሚልቅ እማኞች አመልክተዋል። በቅርቡ እንኳ ቁጥራቸው ከ 2000 በላይ የኦሮሞ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን አገዛዙ በአዲስ አበባ ዙሪያ ሊያደርግ ያቀደውን የመሬት ዘረፋ ጋር በተያያዘ ለእስር ተዳርገው ከፍተኛ ቶርቸር እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ እና ቁጥራቸው ከ 140 በላይ ኦሮሞዎች በአገዛዙ ቅጥረኛ አጋዚዎች በጥይት ተደብድበው መገደላቸው መዘገቡ አይዘነጋም። የፋሽስቱ ወያኔ በኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ላይ እያካሄደ ያለውን አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰትና አፈና ለማስቆም ህዝቡ በብሄር ሳይከፋፈል በጋራ መነሳት እንዳለበትም ተጠቋሟል።

---

# አማራ! አማራ! አማራ! ብቸኛዉ የወያኔ ዘፈን

“ሞኝና ወረቀት የያዙትን አይለቁም” የሚለዉ ቆየት ያለ ያለ የአገራችን ተረት ትርጉም ያልገባዉ ሰዉ ካለ የቅኔ አዋቂ መፈለግ ወይም መጽሐፍ ማገላበጥ የለበትም። ማድረግ ያለበት ቀላል ነገር ቢኖር ወያኔንና የወያኔን ስራ ትኩር ብሎ መመልከት ብቻ ነዉ። በመሠረቱ ወረቀት የያዘዉን አለመልቀቁ ወያኔን ጨምሮ ሁላችንም የምንፈልገዉ ነገር ነዉና ወረቀት ሊመሰገን ይገባል። ሞኝ የያዘዉን አለመልቀቁና ከግዑዙ ወረቀት ጋር መነጻጸሩ ግን ሞኝ አማራጭ የሚባል ነገር የማያዉቅና ግዜና ሁኔታ ሲለዋወጡ ያቿኑ በልጅነቱ የያዛትን አቋም ሙጭጭ አድርጎ እንደያዘ እድሜ ልኩን የሚኖር የሀሳብ ደሃ መሆኑን ያመለክታል። ሞኝን ሞኝ እያለን የምንጠራዉም በዚህ ደካማና ግትር አቋሙ የተነሳ ነዉ። ወያኔ ጫካ ዉስጥ እያለ ለአስራ ሰባት አመት፤ ከጫካዉ ወጥቶ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ደግሞ ለሃያ ሦስት አመታት የያዛቸዉን አቋሞችና የወሰዳቸዉን እርምጃዎች ረጋ ብሎ የተመለከተ ሰዉ ወያኔ፤ ወረቀትና ሞኝ ያላቸዉን የቅርብ ግኑኝነት በቀላሉ መመልከት ይችላል። ሦስቱም አንድ ነገር ከያዙ ሌላ የመያዝ ፍላጎትም ችሎታም የላቸዉም። አዎ! በእርግጥም ሞኝ በሞኝነቱ፤ ወረቀት የተፈጥሮ ጠባዩ በመሆኑ ወያኔ ደግሞ የወረቀትም የሞኝም ጠባይ ስላለዉ ሦስቱም የያዙትን አይለቁም።

የወያኔ መሪዎች ምን ለትግል አነሳሳችሁ ተብለዉ ሲጠየቁ በወጣትነታችን ጠመንጃ ተሸክመን ጫካ እንድንገባ ያስገደደን በወቅቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስር ሰድዶ የነበረዉ የብሄር ብሄረሰቦች ጭቆና ነዉ ብለዉ ነዉ አፋቸዉን ሞልተዉ የሚመልሱት። ዉሸታቸዉን ነዉ። የወያኔ መሪዎች በተለይ ሁለቱ በፀረ ኢትዮጵያ አቋማቸዉ የሚታወቁት መለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ ለትግል ያነሳሳቸዉ የብሄር ብሄረሰቦች ጭቆና ሳይሆን በአማራ ብሄረሰብ ላይ ያላቸዉ ከፍተኛ ጥላቻ ነዉ። ዛሬም አነዚህ ሁለት ፀረ አማራ ግለሰቦች የፈጠሩት ህወሓት የሚባል ዘረኛ ድርጅት ፀረ አማራ ከመሆኑ የተነሳ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በተለየ መንገድ የገባበት ቦታ ሁሉ እየተከታተለ የሚያጠቃዉ ይህንኑ መከረኛ የአማራ ብሄረሰብ ነዉ። ወያኔዎች ለአማራ ብሄረሰብ ያላቸዉን ጥላቻ ላለፉት 34 አመታት በስድብ፤ በንቀትና አማራዉን በጅምላ በማንኳሰስ አሳይተዋል። ባለፉት አስር አመታት ደግሞ አሮሚያ፤ ቤንች ማጂና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዉስጥ የአማራ ተወላጆችን ይህ የእናንተ አገር አይደለምና ወጡ እያሉ አማሮችን ከዉሃ ዉስጥ የወጣ አሳ አድርገዋቸዋል።

ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት በግልጽ እንዳየናቸዉ የወያኔ መሪዎች አማራዉን በመዝለፍና በማፈናቀል ብቻ አልተገቱም፤ ይልቁንም አማራዉን ኢትዮጵያ ዉስጥ ለተከሰቱ ችግሮች ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂ በማድረግ ይህንን በህዝብ ቁጥሩም ሆነ በታሪክ ስፋቱ አንጋፋ የሆነዉን ብሄረሰብ በሌሎቹ የአገራችን ብሄረሰቦች እንዲጠላና በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቅ አድርገዋል። በዚህ የተነሳ ወያኔ ባለፉት ሃያ አራት አመታት ጠፍጥፎ የፈጠሯቸዉ በየክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ምስለኔዎች ምንም አይነት ችግር ባጋጠማቸዉ ቁጥር የችግራቸዉ መንስኤ አድርገዉ የሚወስዱት የአማራዉን ብሄረሰብ ነዉ። ዛሬ በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች፤ ቤንች ማጂና ቤኒሻንጉል ዉስጥ አማራዉን አገርህ አይደለምና ዉጣ የሚባለዉ የዘረኝነት አባዜም ቢሆን የዚሁ ወያኔ ለረጂም አመታት በህዝብ መካከል ሆን ብሎ የዘራዉ ጥላቻ ዉጤት ነዉ።

ወያኔ እራሱን የኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ስርዐት አባት አድርጎ በማቅረብ ብዙ ምዕራባዉያን መንግስታትንና ዋና ዋና ለጋሽ አገሮችን ከጎኑ ማሰለፍ ችሏል። ይህ የማጭበርበር ልምዱ ደግሞ የምርጫ ኮሮጆ እየሰረቀ ተመረጥኩ ያለባቸዉንና ድምጼ ይከበር ብሎ የጠየቀዉን ህዝብ በጥይት የጨፈጨፈበትን ምርጫ አንደ ትክክለኛ ምርጫ አድርጎ ለምዕራባዉያን በመሸጥ ከፍተኛ የገንዘብ ድጎማ አግኝቶበታል። ዘንድሮም ለሚደረገዉ ምርጫ እነዚሁ ምዕራባዉያን አጎሮች በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም በኩል 15 ሚሊዮን ዶላር ወያኔን ለማስታቀፍ ሽርጉድ እያሉ ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ የወያኔ ጥላቻና ዘረኝነት በከፍተኛ ደረጃ ከተንጸባረቀባቸዉ ቦታዎች አንዱና ዋነኛዉ ወያኔ ፈጠርኩት ወይም ጀመርኩት ብሎ የሚነግረን የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ስርዐት ነዉ። በዚህ የወያኔ መድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ስርዐት ዉስጥ በአንድ በኩል ወያኔና ወያኔ በአምሳሉ የፈጠራቸዉ ድርጅቶች አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ በህጋዊ መንገድ የፓለቲካ ፓርቲ ብሎ የመዘገባቸዉ ነገር ግን በጠላትነት ፈርጆ የሚዋጋቸዉ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በስም፤ በስትራቴጂና በአንዳንድ የፖለቲካ አቅጣጫዎች የሚለያዩ ቢሆንም ወያኔ ሁሉንም ትምክተኞች፤ ሽብርተኞች፤ የቀድሞ ስርዐት ናፋቂዎች ወይም የአማራ ልህቃን ፓርቲ እያለ ነዉ የሚጠራቸዉ። በወያኔ ቤት የህወሓትን ዘረኛ አምባገነን ስርዐት አጥብቆ የሚቃወምና ኢትዮጵያዊነትን ደጋግሞ የሚሰብክ ፓርቲም ሆነ ግለሰብ ከየትም ይምጣ ከየት የአማራ ልህቃን ፓርቲ ወይም ትምክህተኛ አማራ ተብሎ ነዉ የሚፈረጀዉ።

ይህ ርካሽና ጎታች የወያኔ ፓለቲካ ወያኔ በአማራ ብሄረሰብ ላይ ያለዉን ስር የሰደደ ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ያለዉን ከፍተኛ ንቀት ያሳያል። ወያኔ የአገሩ አንድነት መደፈርና የሰብዓዊ መብቱ መረገጥ አንገብግቦት “ኢትዮጵያ” “ኢትዮጵያ” እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ የሚያሰማዉን ሁሉ ትምክህተኛ አማራ እያለ በተጣራ ቁጥር ሌሎቹን የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አናንተ ኢትዮጵያዉያን አይደላችሁም ወይም ኢትዮጵያዊነት እናንተ ላይ የተጫነ ዕዳ ነዉ ብሎ እየነገራቸዉ ነዉ። ይህ ክፉና መዘዘኛ የሆነ ፀረ ኢትዮጵያ አባባል ደግሞ በሌላ መልኩ ህገ መንግስቱ ዉሰጥም የተቀመጠ አባባል ነዉ። የወያኔን ህገ መንግስት አንቀጽ 39 በትክክል ከተመለከትነዉ አንቀጹ የሚለዉ ኢትዮጵያዊነትን የማይፈልግ ሁሉ መገንጠልና የራሱን መንግስት መመስረት ይችላል ነዉ ። ወያኔ ሺ ግዜ ቢነግሩት ፍጹም የማይገባዉ የዉኃ ዉስጥ ድንጋይ ስለሆነ ነዉ እንጂ ቢገባዉማ ኖሮ እሱ በነጋ በጠባ ፀረ ኢትዮጵያዊነትን የሚያስተምራቸዉ ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦች ይጠቅመናል፤ ያግባባናል ወይም የኤኮኖሚ ግኑኝነታችንን ያጠናክርልናል ብለዉ የክልላቸዉ የስራ ቋንቋ አድርገዉ የመረጡት አገራችን ዉስጥ የስራና የመግባቢያ ቋንቋ የሆነዉን አማርኛን ነዉ።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በወጣትነታቸዉ የተጠናወታቸዉን ፀረ አማራ በሽታ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለእያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ ለማስተላለፍ ያላደረጉት ነገር የለም። ደግነቱ ግን አንዳንድ እንደነሱ በዘር በሽታ ከተለከፉ ጥቂት ህሙማን ዉጭ የወያኔን ፀረ ህዝብና ፀረ አገር ሃሳብ ተቀብሎ ያስተናገደ ማንም የለም። ሆኖም ወያኔዎች የአገሪቱን የሚድያ ተቋሞች ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጣጠሩ ይህንን ፀረ አማራ ፕሮፓጋንደዳቸዉን ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስታለፈቸዉን እንደቀጠሉበት ነዉ። ባለፉት ጥቂት አመታት በግልጽ እንዳየነዉ ደግሞ ወያኔ ይህንን ፀረ አማራ ዘመቻዉን እስከዛሬ ካስተናገደበት ከአገር አቀፍ መድረክ ወደ አለም አቀፍ መድረክ ይዞት እየሄደ ነዉ። በቅርቡ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ይፋ የሆኑ ሪፖርቶች በግልጽ እንዳሳዩን አንዳንድ ታሪክን አገላብጠዉ ማየት የተሳናቸዉና በተለይም የኢትዮጵያን ማህበረሰባዊ አደረጃጀት በሚገባ ያላጤኑ ሀላፊነት የጎደላቸዉ አለም አቀፍ ተቋሞች ይህንን ወያኔ በግርድፉ የሚያቀርብላቸዉን ፀረ ህዝብ ፕሮፓጋንዳ እንደትክክለኛ መረጃ በመዉሰድ የወያኔ ወጥመድ ዉስጥ ሰተት ብለዉ ሲገቡ ተስተዉሏል።

በያዝነዉ ወር በተመድ የጸጥታ ምክር ቤት ስር የሶማሊያንና የኤርትራን ጉዳዮች የሚከታተለዉ ቡድን ለንባብ ባበቃዉ ሪፖርት ዉስጥ የወያኔን መዝገብ እያገላበጠ ያገኛቸዉን ፍጹም መሠረተ ቢስ የሆኑ መረጃዎች በመጠቀም የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን ስም ሲያጎድፍ ታይቷል። ይህ አለምአቀፋዊ ተቋም ገለልተኝነቱንና አለምአቀፋዊነቱን ዘንግቶ የአንድ ዘረኛ አምበገነን አገዛዝ ቃል አቀባይ በመሆን ከዘረኝነትና ከአምባገነንነት ለመላቀቅ ከወያኔ ጋር ትንቅንቅ ዉስጥ የገባዉን የኢትዮጵያ ህዝብ አሳዝኗል።

ይህ ተጠሪነቱ ለጸጥታዉ ምክር ቤት የሆነዉ ቡድን የተሰጠዉ ሃላፊነት የኤርትራንና የሶማሊያን ጉዳዮች መከታተል ሆኖ ሳለ በሪፓርቱ ላይ በግልጽ እንደታየዉ ግን በወያኔ ትዕዛዝ ግንቦት ሰባትንና በጸባየ ብልሹነታቸዉ ከግንቦት ሰባት የተሰናበቱ ግለሰቦችን ጉዳይ የሪፖርቱ ማዕከል አድርጎ አዉጥቷል።የዚህ ሃላፊነት የጎደለዉ ቡደን ሪፖርት የሚጀምረዉ ግንቦት 7 የታገደ ወይም የተከለከለ ድርጅት ነዉ እያለ ነዉ፤ ሆኖም ማን እንዳገደዉና የት አገር እንደታገደ ምንም ያለዉ ነገር የለም። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በግንቦት 2008 ዓም ከአራቱም ማዕዘናት የነጻነት፤ የፍትህና የእኩልነት ጥማት ባሰባሰባቸዉ ኢትዮጵያዉያን የተመሰረተዉን ግንቦት 7 ንቅናቄ በ2009 ዓም በአማራ ልህቃን የተመሰረተ ድርጅት ነዉ በማለት ወያኔ የሰጠዉን መረጃ ቅንጣት ታክል የማጣራት ስራ ሳይሰራ እንዳለ በሪፖርቱ ዉስጥ አጠቃልሏል። ኤርትራን አስመልክቶ ሪፖርቱ ዉስጥ የተጠቃለለዉን ዘገባ ለማረጋገጥ ሪፓርቱን ለኤርትራ መንግስትና በተመድ ለኤርትራ አምባሳደር ሌኬ ነበር የሚለዉ ይህ አሳፋሪ ቡድን ግንቦት 7ን በተመለከተ ወያኔ ያሳቀፈዉን የዉሸት መረጃ እንዳለ በማቅረብ ተጠሪነቱ ለተመድ የጸጥታዉ ምክር ቤት ሳይሆን ለወያኔ መሆኑን በተግባር አሳይቷል።

ለመሆኑ አንድ የተመድ አካል የሆነ ቡድን በአገሮችና በፓለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ምን አግብቶት ነዉ አንድን ድርጅት የዚህ ወይም የዚያ ብሄረሰብ ድርጅት ነዉ ብሎ ሪፖርት የሚያወጣዉ? ምክንያቱ ሰንካላና መሰረተ ቢስ ቢሆንም ወያኔ ግንቦት 7ን የአማራ ድርጅት ነዉ የሚልበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለዉ፤ የተመድ አካል የሆነ ድርጅት ግን ምን አይነት ምክንያት ቢኖረዉ ነዉ እሱ እራሱ በዘር የተደራጀዉ ወያኔ የአያሌ ኢትዮጵያዉያን መሰባሰቢያ የሆነዉን ግንቦት ሰባትን የአማራ ልህቃን ድርጅት ነዉ ብለህ ዘግብ ሲለዉ አሜን ብሎና ሪፖርት ጽፎ ለአለም ህዝብ ያቀረበዉ?

ወያኔ ግንቦት 7ን ብቻ ሳይሆን አጥብቀዉ የሚቃወሙትንና የዘረኝነት ፖሊሲዉን የሚያጋልጡ ኃይሎችን ሁሉ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወ/ሮ አዜብ መስፍን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መዳከሙ ተሰማ

ምንም አይነት የፖለቲካ ስልጣን ሳይኖራት ባለቤቷ በጠመንጃ ያገኘዉን ኃይል በመተማመን ስትዘርፍ፤ ስትገርፍና ያገኘችዉን ሁሉ ስትዘልፍ የነረችዉ አዜብ መስፍን ከዘረኛዉ ባለቤቷ ሞት በባለቤታቸውን በድንገተኛ ሞት ከማጣታቸው በፊት የፓርላማ አባል የነበሩት ወ/ሮ በኋላ ፈላጊ እንደሌለዉ ዕቃ ተረስታ መቅረቷን ምንጫቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። የሙስናዋ እመቤት በሚል ልዩ መጠሪያ ስም የምትታወቀዉ አዜብ መስፍን ቀድሞዉንም ተገኝታበት ከማታዉቀዉ ፓርላማው እራሷን ማግለሏንና በድርጅታዊ ስራዎች ላይም የምታደርገዉ ተሳትፎ እየተዳከመ መምጣቱን ምንጮቻችን አክለዉ ገልጸዋል። አዜብ መስፍን ባለፈው የአንድ ዓመት ግዜ ዉስጥ በፓርላማው መቀመጫዋ ላይ ታይታ እንደማታዉቅ ለፓርላማው ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገልጸዋል።

መለስ ዜናዊ በሕይወት በነበረበት ወቅት የትግራይ ክልል ካለው 38 የፓርላማ መቀመጫ ሁለቱ በእሱ በራሱና በባለቤቱ እንደ እርስት ተይዞ መቆቱ የሚታወስ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ በ2003 ዓ.ም በስምንተኛው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባዔ ወቅት መለስ ከህወሃት 9 የሥራ አስፈጻሚ አባላት መካከል ባለቤቱን አዜብን በማስመረጥ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ውስጥ ባልና ሚስት አብረዉ መስራታቸዉ የሚታወስ ነዉ። በዚህም አድራጎታቸውም የትግል ጓዶቻቸው ሳይቀር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የቤተሰብ ጉባዔ አደረገው በሚል ውስጥ ውስጡን በከፍተኛ ደረጃ ሲተቹና ሲያወግዟቸዉ ቆይተዋል። መለስ ዜናዊ ባለቤቱን አዜብን ሲያስመርጥ በመተካካት ስም ስለነበር አዜብ የተካቻዉ ነባሮቹን የህወሓት ትጋዮች እነስዩም መስፍንን፣ አባይ ጸሐዬ፣ አርከበ ዕቁባይን የመሳሰሉ የስራ አስፈጻሚና የማዕከላዊ ኮምቴ አባላትን በማባረር መሆኑ ደግሞ በህወሃት ውስጥ ያለመተማመን እንዲፈጠር ምክንያት ከመሆኑም በላይ ጉምጉምታና ኩርፊያ ሰፍኖ ቆይቷል።

አዜብ መስፍን መለስ ከሞተም በኋላ በመጋቢት ወር 2005 ዓ.ም በተካሄደው የህወሃት ጉባዔ በስራ አስፈጻሚነት በመመረጥ በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚነት እስካሁን የቀጠለች ቢሆንም ከዚህ ቀደም በሁሉም ቦታ ጣልቃ እየገባች ከመስመር ዉጭ ሁሉንም የምታዝበትና ያገኘቻዉን ሁሉ የምትዘልፍበት ያልተገራ ባህርይዋ ከቅርብ ገዜ በኋላ መታረም መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል። አዜብ መስፍን ስብሰባዎችን አልፎ አልፎ ከመካፈል ያለፈ እምብዛም ተሳትፎ ስታደርግ አለመታየቷን የጠቀሰው ምንጫችን ፤ ባለቤቷን ተማምና ከዚህ ቀደም ብዙ የጎዳቻቸው ከፍተኛ አመራሮች ይበቀሉኛል በሚል ማለት መጀመሯን ተናግሯል። በቅርቡ ወይዘሮ አዜብ ከኢሳት ሬድዮ ጋር ባደረገችዉ ቃለ መጠይቅ የምትጠየቀዉ ጥያቄ ሲመቻት አዜብ መስፍን ነኝ ጥያቄዉ ሳይመቻት ሲቀር ደግሞ አዜብ አይደለሁም እያለች ብዙ ሰዎችን ማሳቋ ይታወሳል።

### ሰማያዊ ፓርቲ ለኢትዮጵያ ህዝብ የትግል ትብብር ጥሪ አቀረበ

ሰማያዊ ፓርቲ ባሳለፍነዉ ሳምንት ባወጣው መግለጫ የሀገራችን አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከግዜ ወደ ግዜ እየተባባሱና እየከፉ የመምጣታቸውን ያህል ገዢው ፓርቲ ቆም ብሎ ከማሰብ ይልቅ ጭራሽ አገራችንን ሁላችንም ወደ ማንወጣው አዘቅት ውስጥ እየጨመራት ነዉ ካለ በኋላ ይህንን ስርዐት አስገድደን አገራችንን ነጻ ማድረግ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነዉ ብሏል። ኢህአዲግ ከዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ፍፁም በማይጣጣም መለኩ ዜጎችን ለአንድ ሀሳብ ብቻ እንዲገዙ አስገዳጅ መንገዶችን ጭምር በመጠቀም አፋኝ መዋቅሩን በማናለብኝነት እያስፋፋ እንደሚገኝ የሚገልጸው ሰማያዊ ፓርቲ፣ ገዢው ፓርቲ ለማናቸውም አስተዳደራዊም ይሁን ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ሀይልን በመጠቀም ለመደፍጠጥና ለማጥፋት ቆርጦ በመነሳት ፍፁም አምባገነንነቱን ገፍቶበት የበርካቶች ህይወት እንዲቀጠፍ አድርጓል ብሎአል።

ካለፈው ዓመት የክረምት ወራት መጨረሻ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የምርጫ ቅስቀሳ በሚመስል መልኩ ለዜጎች በተሰጠ አስገዳጅ ስልጠና ወደ 1 ቢሊየን የሚጠጋ የህዝብ ሃብት ማባከኑን ፓርቲው ጠቅሶ፣ ሕገ መንግስቱን በሚፃረር መልኩ በሕትመት ሚዲያዎቹ ባለቤቶች፣ አዘጋጆች፣ በጋዜጠኞቹና ሰራተኞቻቸው ላይ ማስፈራራትን ጨምሮ በርካታ ስነ ልቦናዊ ጫና በማሳደሩም በርካቶች ለስደት ሲዳረጉ ጥቂቶች ደግሞ ለእስር መዳረጋቸውን አስታውሷል። ባሳለፍናቸው ሁለት ወራት ብቻ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ዜጎች በመንግስት ሀይሎች ተገድለዋል – ቆስለዋል – ተሰደዋል ያለው ፓርቲው፣ በአጋዴን_ መንግስትን የተቃወሙ ዜጎች ወደ ግጭት እንዲገቡ በሚገፋፋ መልኩ ጥያቄዎቻቸውን በመግፋት በርካታ ዜጎች በመንግስት ሀይሎች ህይወታቸው መቀጠፉን አመልክቷል::

ይህም ሳያንስ ሬሳቸው እንኳን ክብር በሌለው ሁኔታ መሬት ለመሬት መጎተቱን የገለጸው ሰማያዊ ፓርቲ በጋምቤላም በተመሳሳይ መልኩ የህወሓት ሰዎች መሬት በሕገ-ወጥ መንገድ መቀራመታቸውን የተቃወሙ ዜጎች ወደ ግጭት የተገፉበት እና በርካታ የሰው ህይወት የተቀጠፈበት አሳዛኝ ሁኔታ መንግስት የተያያዘው መንገድ ወደ ከፋ ሁኔታ ሀገሪቷን እየወሰዳት ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ብሎአል።"የሀገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት መላው የሀገሪቱ ህዝብ፣ በውጪ የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ለሀገር ተቆርቋሪ ተቋማት እንዲሁም በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ስር ሆናችሁ ለውጥን የምትሹ ወገኖች ሁሉ _ሀገራችንን ወደ አደጋ እየወሰዳት ያለውን አፋኝ ስርዓት በቻላችሁት ሁሉ በመቃወምና ከስርዓቱ ጋር ባለመተባበር በብሔራዊ ደረጃ የሚደረገው ትግል አካል እንድትሆኑ" ጥሪ እናስተላልፋለን ሲል መግለጫውን ቋጭቷል።

## አዲስ አበባ ዉስጥ በሌሊት በሚለጠፉና በሚበተኑ የታቀዉሞ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፍርሃት ድባብ ውስጥ ከቶት እንደሚገኝ ደብዳቤው ያሳያል ሲል የውስጥ ምንጫችን አመልክቷል።

ከበላይ የአገዛዙ ጽ/ ቤት የወረደውን የትዕዛዝ ደብዳቤ ተከትሎ የየ ቀበሌዎቹ ካድሬዎች የተለያዩ ጫናዎችን በነዋሪዎች ላይ ማሳደር መጀመራቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን አገዛዙ ህብረተሰቡን ሰቅዞ ለመያዝ ይረዳው ዘንድ ከጥቂት ወራቶች በፊት ተግብሮት የነበረውንና ያለምንም ውጤት የተበተነውን የ 1 ለ 5 አደረጃጀት በድጋሚ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑ ታውቋል። የአካባቢው ህብረተሰብ ካድሬዎቹ በሚነዙት ዛቻና ማስፈራሪያ ሽብር ውስጥ መግባቱ የተገለጸ ቢሆንም በተለይ የቤት ለቤት አሰሳና ምዝገባ የሚያካሂዱ ካድሬዎች ግን በህብረተሰቡ እየደረሰባቸው ባለው ከፍተኛ ጥላቻና ንቀት ተሸማቀው ስራቸውን በአግባቡ ለመስራት መቸገራቸውን ምንጫችን አመልክቷል። ይህንን ተከትሎም አንዳንድ የአገዛዙ ካድሬዎች ከህብረተሰቡ ጎራ እየተሰለፉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ የሙስሊሙን ጥያቄ በሃይል ለማዳፈን ሙከራ ቢያደርግም ተቃውሞው በተጠናከረና በተደራጀ ሁኔታ ውስጥ ለውስጥ እየተካሄደ መቀጠሉን በተለያዩ ጊዜያት መዘገቡ አይዘነጋም። ከዚህ ቀደም በተለያዩ የክልል ሀተሞችና የአዲስ አበባ አካባቢዎች በሌሊት የተቃውሞ ጽሁፎች ተለጥፈው መታየታቸውን እየተከታተልን መዘገባችን ይታወሳል።

በሌላ ዜና ከሙስናና መልካም አስተዳደር በደሎች ጋር በተያያዘ በትግራይ ክልል ሃገረሰላም ከተማ ህዝባዊ አመጽ መቀስቀሱን ተከትሎ በከተማዋ አሁንም ድረስ ውጥረት መኖሩን ለማወቅ ችለናል። አመጹ የተቀሰቀሰው በከተማው የአገዛዙ ቅጥረኛ ሹማምንቶች ለመንገድ ስራ የተመደበውን ከፍተኛ ገንዘብ በመዝረፋቸውና ከደረጃ በታች መንገድ ለማስገንባት እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመራቸውን ተከትሎ እንደሆነ ተነግሯል። ከዚሁ ከመንገድ ስራ ጋር በተያያዘ የከተማው ካድሬዎች የመስመር ዳር ቤቶች ለማፍረስ በተደረገው እንቅስቃሴ የሰሩት አድሎም ለህብረተሰቡ መቆጣት ምክንያት መሆኑ ተመልክቷል።

ህዝቡ ወደ አመፅ የተሸጋገረው መንገዱ ለመሰራት እንቅስቃሴ መጀመሩን ተከትሎ ሲሆን የከተማዋ ፖሊስ ህዝባዊ አመፁን እንዲበትን በበላይ ቱባ ሹማምንቶች ትዕዛዝ የወረደ ቢሆንም ፖሊስ ምንም አይነት እርምጃ ለመውሰድ ፍቃደኝነት ባለማሳየቱ ልዩ የፌደራል ፖሊስ ወደ ከተማዋ እንዲንቀሳቀስ አስቸኳይ ትዕዛዝ መተላለፉን ለማወቅ ተችሏል። የሃገረሰላም ከተማ ህዝብ በከተማዋ የተደረገውን ዘረፋና ህገ ወጥ ውሳኔ በመቃወም እስከ የበላይ ቱባ ሹማምንቶች ዘንድ ድረስ አቤቱታ ቢያሰማም መፍትሄ አለማግኘቱ የታወቀ ሲሆን አንዳንድ ወገኖች እንደተናገሩት በተለይ በከተማው በተደረገው ከፍተኛ የዘረፋ ሙስና ወንጀል የህወሃት ቱባ ሹማምንቶች ጭምር ተሳታፊ መሆናቸው ለችግሩ መወሳሰብ ምክንያት መሆኑ ተነግሯል። ህዝባዊ አመጹ ወደ ከፍተኛ ግጭት ሊያመራ እንደሚችልም ተመልክቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## አማራ! አማራ! አማራ! ብቸኛዉ የወያኔ ዘፈን

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሽብርተኛ፤ ትምክህተኛ ወይም ስልጣን ናፋቂ አማራ እያለ ነዉ የሚጠራቸዉ። በወያኔ ቤት የኢትዮጵያን አንድነት የሚሰብክ ሁሉ ትምክተኛ አማራ፤ የሙብት፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ጥያቄ የሚያነሳ የድሮዉን ስርዐት ናፋቂ፤ እኩልነትንና ፍትሃዊነትን እየዳሰሰ የሚጽፍ ጋዜጠኛና ጦማሪ ደግሞ ሽብርተኛ ነዉ። አማራንና የአማራን ባህል ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳዉ ወያኔ የእያንዳንዱ ችግር መንስኤ አማራ ነዉ ብሎ ቢናገር ብዙ አይገርመንም። ከጄኔራል ሳሞራ የኑስ እስከ ጄኔራል ታደሰ ወረደ፤ ከስዩም መስፍን እስከ አባይ ፀሐዬ፤ ከሟቹ መለስ ዜናዊ ጃጅቶ የባጥ የቆጡን እስከሚቀባጥረዉ  ስብሃት ነጋ ድረስ ሌላ ዘር ሳይደባለቅበት በትግራይ ልጆች ብቻ የተሞላዉ ህወሓት የዘረኝነት ካባ ተከናንቦ አንድ አገር ህዝብ ሲያስርና ሲገድል በአይናቸዉ የሚያዩ ሰዎች ኢትዮጵያዉያንን በዘርና በቋንቋ ሳይሆን በፖለቲካ አስተሳሰባቸዉና በአገር ወዳድነታቸዉ ብቻ ያሰባሰበዉን ግንቦት ሰባትን ወያኔ በሉ ስላላቸዉ ብቻ የአማራ ልህቃን ፓርቲ ነዉ ማለታቸዉ ግን እጅግ በጣም ይገርማልም ያሳዝናልም።

የወያኔን ዘረኛ ስርዐት ለማጥፋት የምንታገል ኢትዮጵያዉያን በሙሉ ይህንን ወያኔ "የአማራ ልህቃን" በሚል ቅኝት ቃኝቶ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ የለቀቀዉን ነጠላ ዜማ በሚገባ ልንቃኘዉና ማርከሻዉን ልናዘጋጅለት ይገባል። ወያኔ አገር ቤት ዉስጥ እስከዛሬ ካጋጠመዉ መዐት ሁሉ ጋር በማያያዝ ያሰራጨዉ ፀረ አማራ ፕሮፓጋንዳ አገራችን ኢትዮጵያን ምን ያክል እንደጎዳት አይተናል። ዘንድሮ ወያኔ ጭራሽ ብሶበት አማራንና ሽብርተኝነትና ከስልጣን ጥማት ጋር በማያያዝ አለም አቀፉን ህብረተሰብ አማራን አንድ በሉልኝ እያለ ነዉ። "ሳይቃጠል በቅጠል" እንዲሉ ይህንን ለጆሮ የሚቀፍ የወያኔ ነጠላ ዜማ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት አሁኑኑ ማጥፋት አለብን። የወያኔን ፀረ አማራ ዘመቻ እንደ ፀረ ኦሮሞ፤ ፀረ ሶማሌ፤ ፀረ ትግራይ ፀረ ሲዳማና ባጠቃላይ እንደ ፀረ ኢትዮጵያ ዘመቻ አድርገን በማየት  ሁላችንም እንደ አንድ ሰዉ ቆመን መዋጋትና ማክሸፍ አለብን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!**